# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት — ሁለተኛ

[1]ሽማግሌው፤

በእውነት ለምወዳት እኔ ብቻ ሳልሆን
እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ለሚወዷት ለተ
መረጠችው እመቤትና ለልጆቿ፤ [2]በውስጣ
ችን ከሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ከሚሆን
እውነት የተነሣ፣ [3]ከእግዚአብሔር አብና የአብ
ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ ምሕረ
ትና ሰላም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር
ይሆናል።

[4]ከልጆችሽ አንዳንዶቹ ከአብ በተሰጠን
ትእዛዝ መሠረት በእውነት ጸንተው እየሄዱ
በማግኘቴ እጅግ ደስ ብሎኛል። [5]አሁንም
እመቤት ሆይ፤ ከመጀመሪያ የነበረችውን
እንጂ አዲስ ትእዛዝ አልጽፍልሽም፤ ይኸ
ውም እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው።
[6]ይህም ፍቅር፤ በትእዛዙ መሠረት እንመላለስ
ዘንድ ነው። ትእዛዙም ከመጀመሪያ እንደ
ሰማችሁት በፍቅር እንድትኖሩ ነው።

[7]ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማ
ያምኑ ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ወጥተዋል።
እንዲህ ያለ ማንኛውም ሰው አታላይና የክር
ስቶስ ተቃዋሚ ነው። [8]እናንተም የደከማ
ችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ
ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።
[9]በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህ
ርቱ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም፤ በክር
ስቶስ ትምህርት የሚኖር ግን አብም ወል
ድም አለው። [10]ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ፣
ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ
አትቀበሉት፤ ሰላምም አትበሉት፤ [11]የሚቀ
በለው ሰው፣ የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆና
ልና።

[12]የምጽፍላችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ፤
ይሁን እንጂ በወረቀትና በቀለም እንዲ
ሆን አልፈልግም፤ ዳሩ ግን ደስታችን ፍጹም
ይሆን ዘንድ ወደ እናንተ መጥቼ ፊት ለፊት
ላነጋግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

[13]የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላ
ምታ ያቀርቡልሻል።

1፥1 ቆላ3፡13፤
ዮሐ8፥32፤
ሐሥ11፥30፤
ሮሜ16፥13፤
1ጢሞ 2፥4፤
1ጴጥ5፥13፤3ዮሐ1
1፥2 ዮሐ14፥17፤
2ጴጥ1፥12፤1ዮሐ1፥8
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ዮሐ3፥4
1፥5 1ዮሐ2፥7
1፥6 ዮሐ14፥15፤
1ዮሐ2፥5፡7
1፥7 ዮሐ1፥14፤
1ዮሐ2፥18፡22፤
4፥1፡2፡3
1፥8ማቴ10፥42፤
ማር 10፥29፡30፤
1ቆሮ3፥8፤ዕብ10፥35፡
36፤11፥26
1፥9 ዮሐ8፥31፤
1ዮሐ2፥23
1፥10 ሮሜ16፥17
1፥11 1ጢሞ5፥22
1፥12 ዮሐ3፥29፤
3ዮሐ13፡14
1፥13 ቆላ1